## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

### የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያዎች

1. በተለያየ ምክኒያት ወደኋላ የተመለሱ ወገኖችን ለመፈለግና ለመጎብኘት ሽማግሌዎች እቅድ አውጥተው እየተንቀሳቅሱ ስልሆን የምናውቀውና መጎብኘት አለበት የምትሉትን ስም ለወንድም ጌቱ እንድትሰጡ እናሳስባለን።

2. በቤተክርስቲያናችን በለዩ ልዩ አገልግሎት ውስጥ ያላችሁ አገልጋዮች በሙሉ ቀጥሎ በተገለጹት ቀናት ከእሁድ አምልኮ ፕሮግራም በኋላ ከሽማግሌዎች ጋር ስብሰባ ስለሚኖረን በጊዜ ሰሌዳችሁ መሰረት እንድትገኙ በጌታ ፍቅር እናሳስባለን።

- ⇒ ሜይ27/218 ዲያቆናት
- ⇒ ጁን3/2018 ህንጻ ኮሚቴ
- ⇒ ጁን10 /2018 ወንጌል ስርጭት
- ⇒ ጁን17 /2018 ኳየር በሙሉ
- ⇒ ጁን24/2018 ከጸሎት አገልጋዮች
- ⇒ ጁላይ1 /2018 የቤት ለቤት ህብረት መሪዎች
- ⇒ ጁላይ8/2018 የልጆች አገልግሎት
- ⇒ ጁላይ15/2018 ኮሚኒኬሽን ሚዲያ
- ⇒ ጁላይ22/218 የእህቶች አገልግሎት
- ⇒ ጁን29/2018 ርህራዬ አገልግሎት



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

# የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




**"እመን ብቻ እንጂ አትፍራ።"**
(ማር. 5:36)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**June 17, 2018** | **ሰኔ 10፣ 2010 ዓ.ም.**

# የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም ሰለሞን ወመነ |
| አምልኮ....................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ሰለሞን ወመነ |
| ቃል ............. | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

"እንግዲህ፡- ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና። ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።" (ማቴ. 6፡ 31-33)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አሰፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመነ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ግርማ ካሳ

## ተባርከናል!

*"በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።" (ኤፌ. 1፡3)*

ምድራዊ ሕይወት በረከትን ለመያዝ የሚደረግ ሩጫ የበዛበት ነው። ሰዎች የባለጠግነትን በረከት ለማግኘት ይጥራሉ፤ ዝናንም ለማግኘትም ብዙ መንገድ ይሄዳሉ፤ የስልጣንምም እርከን ለመውጣት ብርቱ ፍልሚያ ያደርጋሉ። በብዙ ሃይማኖቶችም ሰዎች የጽድቅን በረከት እንዲያገኙ ስረአቶችን ለመፈጸም ይታገላሉ። ሰው በራሱ በረከትን ለማግኘት የሚያደርገው መውተርተር የበረከት ጫፍ ላይ አድርሶ የሚሳርፍ አይደለም። ይልቁንም በብርቱ ጥረትና ግረት የያዙት በረከት ሲጨብጡት ምንም እየሆነባቸው ሌላ ከፍ ያለ የበረከት መሰላል ላይ ለመውጣት ያልማሉ። ፍላጎታቸውም እንደ ሚሸሽ ኢላማ ከፊታቸው እያመለጠ ይቀድማቸዋል። አንድ ጊዜ እውቁ ቱጃር ጃን ዲ ርክፌለር ለአንድ ሰው ምን ያህል ገንዘብ ይበቃዋል ተብለው ሲጠየቁ "ባለህ ላይ ጥቂት ሲጨማር" በማለት መመለሳቸው ይነገራል። ምድራዊው ሰው ሁልጊዜ ባለው ላይ ጥቂት መጨመር ይፈልጋል። የፈለገውን "ጥቂት" ሲጨምር ደግም ሌላ "ጥቂት" መጨመርን ይሻል። እንዲህ እያለ ሰው የማይሞላ የበረከት ቋት ሊሞላ ሲዳክር ሕይወቱን ይፈጃል።

ክርስትና ግን የሚጀምረው "ትባረካለህ" ብሎ ሳይሆን "ተባርከሃል" ብሎ ነው። ክርስትና በረከትን የመፈለግ ሩጫ ሳይሆን እንደተባረከን ተረድተን፤ የበረከታችንን ጥልቀትና ብዛት እየተረዳን በምድር እግዚአብሔር እንድፈጽመው የሰጠንን ስራ እየሰራን መኖር ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር እስራኤልን "አንተ ብሩክ ነህ፣ እግዚአብሔር ያዳነው ሕዝብ እንዳንተ ያለ ማን አለ?" (ዘዳ. 33፡29 አ.መ.ት.) ይለዋል። የእስራኤል በረከት የእርሱ ጥረት ውጤት ሳይሆን በእግዚአብሔር የመመረጡ ጉዳይ ነው። የሕዝቡ በረከት እርሱ እራሱ እንጂ በእርሱ ያገኙት የምድር በረከት አልነበረም። ስለዚህም "መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው፤ የዘላለምም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው" ይለዋል። (ቁ. 27) አዲስ ኪዳንም የሚያስተምረን እግዚአብሔር "በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ" በሰማያዊ ስፍራ እንደ ባረከን ነው። አሁን ተባርከናል! ከዚህ በኋላ የሚያስደንቀን ነገር ቢኖር የበረከቱ መገለጥ ነው። የተባረክንበት የበረከት ጥልቀት አሁን ካለን የመረዳት አቅም የሚያልፍ ነው። ነገር ግን አንድ ነገር እናውቃለን። እኛ በረከትን ለማግኘት የምንውተረተር አይደለንም። በክርስቶስ ተባርከናል። የምድር ሁኔታችን ምንም ይሆን ምን የተባረከን ሰዎች ነን። በረከታችን እሩሱ እራሱ ነው። ለዚህም ቃሉ እርሱን ማለትም መንግስቱንና ጽድቁን እንድንሻ ይመከረናል። በሰማይ በረከት የባረከን አምላክ በሚያስፈልገን የምድር በረከት አያጎድለንም። ምድራዊው ነገር ቢጎድልም እንኳ እንባቆም እንደዘመረው መንፈሳዊ በረከታችንን እያየን በመስጋና ሙላት ውስጥ እንዳንገባ አይከለክለንም።

ወገኖቼ፡- የተባረከ ሕዝብ አመስጋኝ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ ምንም እንኳ ይህንን መልዕክት ሲጽፍልን በእስር ላይ ቢሆንም "የባረከን ይባረክ" ብሎ ለምስጋና ይጋብዘናል። እግዚአብሔር አምላኩ የሆነለት ሕዝብ ብሩክ ነው፤ የበረከት ቁንጮ ላይ ደርሷል፤ የበረከቱን አምላክ በምንም ሁኔታ ያከብራል።